# የመላው ዐማራ ሕዝብ ፓርቲ
# All Amhara People's Party

Telephone: +251920126061 Email: aapoallamhara@gmail.com Website: www.aapo-mahd.org


**ቁጥር፡ መዐሕፓ/003/2011** **ቀን፡ ፳፩/፲/፳፻፲፩ ዓ.ም**

## በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከመዐሕፓ የተሰጠ መግለጫ

**አርብ ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ እና በአዲስ አበባ የተከሰተው ክስተት በእጅጉ አሳዛኝ ነው። በተለይ ባህር ዳር በወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመው ግድያ የዐማራን ህዘብ በእጅጉ ያሳዘነ ነው። ይህ የዐማራ ሕዝብ ፍጅት ቀጣይ ክፍል የሆነ ድርጊት የዐማራ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመው ዕልቂት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መምጣቱን የሚያስረዳ ነው። ይህ ድርጊት ከፍተኛ ዝግጅትና ጥንቃቄ የተደረገበት ብዙ ዓላማ ያዘለ ፀረ-ዐማራ የሆነ እንቅቃሴ ነው።

ከዓላማዎቹ አንዱ ምልክት የነበሩትን ሰዎች በተለያየ መንገድ እንዲያጣ የተደረገው የዐማራ ሕዝብ መሪዎቼ የሚላቸው እና ምልክት እየሆኑ የመጡ መሪዎች ሲመጡ እነሱን በመግደል ህዝቡን መሪ ማሳጣት ሲሆን ይህም ኩነት በተመሳሳይ ሴራ የተሰውትን ታላቁን የዐማራ ሰማዕት ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን እንድናስታውስ አድርጎናል። ይህ ፀረ-ዐማራ ግድያ መፈፀሙ ሳያንስ ሁኔታውን በወንድማማች መካከል እርስ-በርስ የተደረገ በማስመሰል ጉዳዩን አንድም ዐማራውን በሀሳብ ለመከፋፈል ብሎም ህዝቡን በጎጥ ለመከፋፈል የተደረገ ዕኩይ ተግባር መሆኑ ነው። የነዚህ ኃይሎች እንቅስቃሴ ይህን ክስተት በመጠቀምና ሰበብ በማድረግ አስቀድመው ያሴሩባቸውን የዐማራ ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶች እና ተሟጋቾች ማሰር፣ ማንገላታት፣ ማሸማቀቅ እና መግደል ሁለተኛው ጉዳይ ሲሆን፤ ይህንንም ካደረጉ በኋላ ለዐማራ የሚቆሙ ታጋዮችን ወይም ድርጅቶችን ጨርሶ ለማጥፋት ወይም በእጅጉ ለማዳከም የታለመ እንደሆነ እናምናለን። እነዚህ ኃይሎች ይህም ሳይበቃቸው በተደጋጋሚ በግልጽ የምናውቀውን ዐማራው በብዛት የሚኖርበትን "የዐማራ ክልል" የጦርነት አውድማ በማድረግ ህዝቡን አስከተቸቻላቸው ድረስ እርስ-በርስ ተዋግቶ እንዲጠፋፋ ካልሆነም እነዚሁ ኃይሎች ክልሉን በይፋ ለመውረር የሚደረግ ዝግጅት መሆኑን እንገነዘባለን። በነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የሥነ-ልቦና ጫና በማድረስ ዐማራን እንደሕዝብ አንገት ለማስደፋት ቀጥሎም ክልሉን ለመቆጣጠር እና ለመበዝበዝ ዓላማ እንዳለ እንገነዘባለን።

መንግሥት ከማንም በላይ ኃላፊነት የሚሰማው እና ሀገርንም የማረጋጋት ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለሕዝብ ከሚበጀው የማረጋጋት ሥራ ይልቅ ከመንግሥት አካላት የማይጠበቁ አደናጋሪ እና የተደበላለቁ መግለጫዎች ህብረተሰቡን ከማረጋጋት ይልቅ ቁጭት ቀስቃሽ ሆነው አግኝተናቸዋል። በመሆኑም መንግሥት ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብ እናሳስባለን።

መንግሥት አጋጣሚውን ለራሱ የፖለቲካዊ ፍጆታ በመጠቀም ይቃወሙኛል የሚላቸውን አክቲቪስቶች እና ጋዜጠኞችን ለማፈንና ለማሰር ብሎም አንዳንዶቹን በአፋኝነቱ በሚታወቅበት እና "መደርደሪያው ሰቅሎት የነበረውን የፀረ-ሽብር ሕግ" በማንሳት እነዚህን ወንድሞች ለማፈን የሄደበት ርቀት በእጅጉ የሚያሳዝንና ቀጣይ የዴሞክራሲ ጉዟችንም ምናልባትም ቀድሞ ከነበረው ወደባሰ አዘቅት እንዳይሄድ ያሳስበናል።

ሰኔ 15 የተፈጠረው አሳዛኝ ድርጊት ሳያንስ በኢትዮጵያ የተለያዩ ክፍሎች በተለይ በአዲስ አበበ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ ከተሞችና ሌሎች የኦሮሚያ ክልል ቦታዎች የተወሰኑ የሌሎች ብሔር ተወላጆችን ጨምሮ

Telephone፡ +251920126061 Email፡ aapoallamhara@gmail.com Website፡ www.aapo-mahd.org

በርካታ የዐማራ ተወላጅ ግለሰቦች እና ባለሀብቶች ላይ ያነጣጠረ የማሰር ሥራ እንደቀጠለ መገንዘብ ችለናል፡ ፡ ይህም መዐሕፓን በእጅጉ ያሳስበዋል፡፡ ስለሆነም፡-

- ይህ በእጅጉ ታቅዶበት የተከወነ ፀረ-ዐማራ ሴራ ዐማራው እያደረገ ያለውን የኅልውና ትግል ቀጥታ ውጊያ በመክፈት የማዳፈንና ዐማራነትን የማጥፋት ሴራ መሆኑን ሁሉም ዐማራ ተረድቶ የዐማራ ሕዝብ በጠላት የመጥለፊያ አጀንዳ ተጠልፎ ሳይወድቅ ከምን ጊዜም በላይ በዐማራዊ አንድነት እንዲቆም በድጋሚ ጥሪ እናቀርባለን፡፡
- የዐማራ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የማህበረሰብ አንቂዎችና ሌሎችም አከላት ተባባብረን እንድንሰራ እና በጋራ እንድንቆም እንጠይቃለን፡፡
- በመላው ዓለም ያላችሁ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ከዐማራ ሕዝብ ጎን እንድትቆሙ እንጠይቃለን፡፡ በተለይ ጋዜጤኞች የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ በመሥራት የችግሩን ምንጭ እና የተደረገውን ሴራ በማጋለጥ ከሕዝብ ጎን እንድትቆሙ እንጠይቃለን፡፡
- መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል ብቻ የሚነዛውን ከአመክንዮ የራቀ ትዝብት ላይ የሚጥል ቅስቀሳ ወደ ጎን በመተው በግልጽ ጥቃት ከተፈጸመበት የዐማራ ሕዝብ ጎን እንዲቆም በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡
- መንግሥት በማን አለብኝነት የሚገልፃቸውን ዐማራን ለመከፋፈል ሆን ተብሎ በሚመስል መልኩ የተላለፉ መግለጫዎችን የወንጀል ምርመራው በአግባቡ ተደርጎ ውጤቱ ለሕዝብ ይፋ ከመደረጉ በፊት ከመግለጽ እንዲቆጠብ እናሳስባለን፡፡
- መንግሥት የሚያወጣቸው እርስ በእርሳቸው የተምታቱ መረጃዎች፣ በቂ ምርመራ ሳይደረግ አስቀድሞ ያደረጋቸው ፍረጃዎች እንዲሁም ሌሎች ሁኔታዎች ተደምረው መንግሥት ጉዳዩን በትክክል የመመርመሩን ሁኔታ በእጅጉ ስለምንጠራጠር ገለልተኛ አጣሪ አካል ተሰይሞ ክስተቱን እንዲመረምር እንዲደረግ እንጠይቃለን።
- መንግሥት በቁጥጥር ስር ስለዋሉ ግለሰቦች ብሎም ስለአጠቃላይ የምርመራው ሂደት ለሕዝቡ ዝርዝር እና በቂ መረጃ እንዲሰጥ እናሳስባለን፡፡
- መንግሥት አጋጣሚውን ተጠቅሞ በመንግሥት የአመራር መዋቅር ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉ የዐማራ ተቆርቋሪዎችን ለማሰር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ያለ ስለሚመስል መንግሥት ከዚህ ድርጊቱ በአስቸኳይ እንዲቆጠብ እንዲሁም አሁንም በቁጥጥር ሥር የዋሉ ተጠርጣሪዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮ እንዲያዙ እንዲሁም ሕጉ ባስቀመጠው የ48 ሰዓታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ እናሳስባለን።
- የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተፈጠረው ችግር ከአቅሙ በላይ አለመሆኑን ግልጽ ማረጋገጫ እንዲሰጥና ሕብረተሰቡን እንዲያረጋጋ እናሳስባለለ፡፡
- መላው የዐማራ ሕዝብ አሁንም በየቦታው የሚነዛውን የአሉባልታ ወሬ ችላ በማለት ሰኔ 15 የተፈጠረው ችግር ትክክለኛ መንስዔ ምን እንደሆነ፣ ከዚህ ድርጊት ጋር ተያይዞ በተከታታይ የተፈጠሩትን ሁኔታዎች እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ግልጽነት ያለው ተጨባጭ ሪፖርት

Telephone፡ +251920126061 Email፡ aapoallamhara@gmail.com Website፡ www.aapo-mahd.org

**እስኪቀርብ አሁንም በመረጋጋት እንዲቆይ እንጠይቃለን፡፡ መዐሕፓ ጉዳዩን በአጽንዖት እየተከታተለው መሆኑን ለመላው ሕዝባችን በድጋሚ ለማሳወቅ እንወዳለን።**

- **ዐማራን እርስ በእርስ ለማበጣበጥ እና ማኅበራዊ ሰላም ለመንሳት የምትረረጡ ኃይሎች ከዚህ ቅዠታችሁ እንድትታቀቡ እናስገነዝባለን፡፡**

**ዐማራ በልጆቹ ትግል ታሪኩን ያድሳል !**

**ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል - ኪዳን ነው !**